ባሸዋምአፀደ ሕፃናት የመጀመሪያ፣ ከፍተኛና የመሰናዶ ት/ቤት

የ2012 ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ለ9ኛ ክፍል የተዘጋጀ

መመሪያ አንድ፡- ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው ከቀረቡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

———1. ከሚከተሉት የዘይቤ አይነቶች ማወዳደሪያ ቃላትን የሚጠቀሙ የቱ ነው?

ሀ. ሰውኛ ዘይቤ ለ. አነፃፃሪ ዘይቤ ሐ. ለዋጭ ዘይቤ መ. ግነት ዘይቤ

———2. በጎቹን ከ——— አውጥቶ እየነዳ ወደ ሜዳ ሄደ፡፡ በባዶ ቦታው ላይ መግባት ያለበት የቱ ነው? ሀ. ጋጣው ለ. ጉሮኖው ሐ. ከበረቱ መ. ከጎጆው

———3. አንድ ስንኝ በምጣኔ ተሳክቶ ሲጨርስ ——— ይበላል፡፡

ሀ. ቤት መታ ለ. ቤት ፈረስ ሐ. ቤት መ. ቤት ደፋ

———4. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ስማዊ ሀረግ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ልጇ ዛሬ ሐ. ልጇ ዛሬ ጠዋት ቁርሷን

ለ. ልጇ ዛሬ ጠዋት መ. ልጇ ዛሬ ጠዋት ቁርሷን በሳህን

———5. ከሚከተሉት ውስጥ ለዋጭ ዘይበየ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. እንደ ማር ጣፋጭ ለ. አባቱን ይመስላል ሐ. የዘንባባ ማርነሽ መ. ቁስሉ አፍን ከፍታ

———6. ልጅቷ የግቢውን በር ቀጠቀጠችው በዚህ አ.ነገር ውስጥ ተሳቢው የቱ ነው?

ሀ. ልጅቷ ለ.የግቢውን ሐ. የግቢውን በር መ. ቁጦቁጦቸው

———7. እልም የለውሸት የሚል ፍቺ ያለው ፈሊጣዊ አነጋገር የቱ ነው?

ሀ. ፈጀችው ለ. በሬ ወለዴ ሐ. አፍን አሟሽ መ. ወረዛ

———8. ከሚከተሉት ሰውኛ ዘይቤ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ለአህያ ማር አይጥማትም ለ. ፍየል በልታ በበግ አበሰች ሐ. ቀኑ ተክዟል መ. ሁሉም

———9. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስብስብ ዐ.ነገር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በጨርቅ አፍን ሸፈነ ሐ. ዝሆን ግዙፍ እንስሳ ነው

ለ. ልጁ ብዙ ጥያቄ ጠየቀችኝ   መ. የታመመው ውሻ ተደብድቦ ሞተ

———10. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የቃል ክፍሉ የተለየው የቱ ነው?

ሀ. ነገረኛ   ለ. ታታሪ   ሐ. ፈጣን   መ. ክፉኛ

———11. ነፈገ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. በታተነ   ለ. ለገሰ   ሐ. ከለከለ   መ. ዘራ

———12. የአንድን ነገር ምንነት፣ ቅርፅ፣ የአሰራር ቅደም ተከተል ጥቅምና ጉዳት የሚዘረዝርበት የድርሰት አይነት——— ይበላል።

ሀ. አስረጂ ድርሰት   ለ. አመዛዛኝ ድርሰት   ሐ. ተራኪ ድርሰት   መ. ሀ ና ሐ መልስ ይሆናል

———13. አቅጣጫ የሚጠቁም ሀሳብ ያለው ሀረግ የቱ ነው?

ሀ. ረዥም ጠጉር ያላት   ሐ. በፊትለፊትና በስተጓዳ

ለ. ወጪ ገቢውን የሚታዘብ   መ. ድንክዬ ጠረጴዛ

———14. እኔ <u>ሽቅብ</u> ሰወጣ እሱ ግን ——— ወረዱ።

ሀ. ቁልል   ለ. ወደ ላይ   ሐ. ቁልቁል   መ. ዳገት

———15. ሁኔታን የሚገልፅ ሀሳብ ያለው ሀረግ የቱ ነው?

ሀ. ተሰርቶ ሲያልቅ   ለ. እየተክለፈለፈ   ሐ. በመገባደጀው   መ. ሶፋውስር

———16. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የተለየው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ሞፈር   ለ. ድግር   ሐ. ቀንበር   መ. ደጋን

———17. መጠንን የሚገልፅ ሀሳብ ያለው ሀረግ የቱ ነው?

ሀ. የሚሯሯጡ   ለ. በረከት ያለሰው   ሐ. ከህንፃው አጠገብ   መ. ደስተኛ ፊት

———18. "አታላዮች" በሚለው ቃል ጥገኛ ምዕላዱ የቱ ነው?

ሀ. አታሎ   ለ. -ኦች   ሐ. -ዎች   መ. አታላይ

———19. በተውኔት ውስጥ ——— ገፀባህሪያት የሚካውኑት ምክንያትና ውጤትን ይወክላል።

ሀ. ታሪክ ለ. ትልም ሐ. መቼት መ. ግጭት

———20. ከሚከተሉት መካከል የቃል ክፍሉ ተውሳከ ግስ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ወደ ለ. ነገረኛ ሐ. ዜና መ. ቶሎቶሎ

<u>*መመሪያ ሁለት፡- በተራ ቁጥሩ ትክክል ከተዘረዘሩት ቃላት መካከል በፍቺ የማይመሳሰለውን አንድ ቃል ምረጡ*</u>

———21. ሀ. ገሰሰ ለ. ለበጠ ሐ. ሸፈነ መ. ጠረዘ

———22. ሀ. መረን ለ. ባለጌ ሐ. ልቅ መ. ታጋሽ

———23. ሀ. አቀበት ለ. መስክ ሐ. ሜዳ መ. መሬት

———24. ሀ. ተደራሲ ለ. አድማጭ ሐ. ተመልካች መ. ተራኪ

———25. ሀ. ማድቀቅ ለ. ማጨቅ ሐ. መጠቅጠቅ መ. ማመቅ

———26. ሀ. ባርኔጣ ለ. ግልድም ሐ. ኮፍያ መ. ቆብ

———27. ሀ. አባይ ለ. ውሸታም ሐ. አዋኪ መ. ቀጣፊ

——-28. ሀ. ነደለ ለ. ቀደደ ሐ. በሳ መ. ጠቀመ

<u>*መመሪያ ሶስት ፡-ለቀረቡት ዘይቤዎች ከተሰጡጥ አማራጭ የዘይቤ አይነቶች ተስማሚውን ምረጡ፡፡*</u>

——-29. እንደገበቴ ውሃ አይንህ ይዋልላል

ሀ. ለ. አነፃፃሪ ዘይቤ ሐ. እንቶኔ ዘይቤ መ. ግነት ዘይቤ

——-30. የዘንባባ ማርነሽ

ሀ. እንቶኔ ዘይቤ ለ. ሰውኛ ዘይቤ ሐ. ግነት ዘይቤ መ. ለዋጭ ዘይቤ

——-31. ተናገር አንተ ሀውልት?

ሀ. እንቶኔ ዘይቤ ለ. አነፃፃሪ ዘይቤ ሐ. ለዋጭ ዘይቤ መ.

——-32. አገጬ መሬት ሊነካ ምንም አልቀረውም፡፡

ሀ. ግነት ዘይቤ ለ. ሰውኛ ዘይቤ ሐ. ተምሳሌት ዘይቤ መ. እንቶኔ ዘይቤ

——-33. ጅብ የማያውቁት ሀገር ሄደ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ፡፡

ሀ.እንቶኔ ዘይቤ ለ. ሰውኛ ዘይቤ ሐ. ለዋጭ ዘይቤ መ. አነፃፃሪ ዘይቤ

——-34. ሰውነቱ እሳት ሆነ፡፡

ሀ. ሰውኛ ዘይቤ ለ. አነፃፃሪ ዘይቤ ሐ. ለዋጭ ዘይቤ መ. ኩሸት/ግነት ዘይቤ

——-35. ንፋሱም ይናገር፣አይኔን ያበሳጨው፣

ካፋፍ ላይ ቆሜ ቀልቤን ያታለለው፡፡

ሀ. ሰውኛ ዘይቤ ለ. ግነት ዘይቤ ሐ.አነፃፃሪ ዘይቤ መ. ተምሳሌት ዘይቤ

መመሪያ አራት፡- ***ከታች ለቀረቡት ቅኔዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ወርቁን የያዘውን ፊደል ምረጡ***

——-36. ስጋ አበላ ብዬ የቆረጥኩትን፣

ላሳያችሁ መጣሁ እኔማ ጣቴን፡፡

ሀ. ማጣቴን ላሳያችሁ መጣሁ ሐ. ስጋ መብላት ፈለኩኝ

ለ. ጣቴን ተቆረጥኩ መ. ማጣቴን

——-37. ከልፍኝ አስወጥተው እዳስ አጉረው፣

ቅራሬውን ስጡኝ ጠላነው ብለው፡፡

ሀ.የሚጠጣ ጠላ ስጡኝ ለ. ቅራሬ ስጡን ሐ. ጠልተውኛል መ. ገፍተው አስወጡኝ

——-38. ፈረስ አገኘሁ ከወንድሜ፣

ኮርቻ አጣሁ ደግሜ፡፡

ሀ. ወንድሜ አጣሁ ለ. ኮርቻ አጣሁ ሐ. ኮርቹ ነበር አሁን አጣሁ መ. ደከምኩ

——-39. አልተከልኩ እንኳ ከጓሮዬ፣

ዱባ ለመከራዬ፡፡

ሀ.ዱባ ለመከራ ይጠቅማል ሐ. ዱባ ተክዬ ነበር

ለ. በድንገት መከራ ገጠመኝ መ. ከጓሮዬ ዱባ የለም

——-40. ጤፍን ዳዋ በላው ቀለባችንን፣

አንቺ ሰው አርሚ እንጣላለን።

ሀ. አርሚ ባክሽ ለ. ፀባይሽን አስተካከይ ሐ. ጤፉን ዳዋ በላው መ. ጤፉን አርማው